# በሜልበርን የኢሣት ዕርዳታ ማሰባሰቢያ ዝግጅት
# በስኬት ተጠናቀቀ!

"ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ቡድን በሜልበርን" የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን(ኢሣት)ን ለመርዳት በማሰብ ያዘጋጀው የዕርዳታ ማሰባሰቢያ የራት ምሽት ባለፈው ቅዳሜ ኦገስት 28 ቀን በርካታ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት ተከናውኖ በስኬት ተጠናቋል።

በአሁኑ ሰአት በመላው አለም የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ኢሣት ላቀረበው ዓለም አቀፍ የትብብር ጥሪ! ምላሽ ለመስጠት እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ይታወቃል። የዚሁ አለም አቀፍ እንቅስቃሴ አካል የሆነው የሜልበርኑ የዕርዳታ ማሰባሰቢያ ዝግጅት የተጀመረው በዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ቡድን ሰብሳቢ በአቶ አበበ ጽጌ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ነበር።

አቶ አበበ ባሰሙት ንግግር ነጻ-ሚዲያ በአንድ ሃገር ሁለንተናዊ እድገትና ለህዝቦች ማህበራዊ ሕይወት መሻሻል የሚጫወተውን ግዙፍ ሚና ገልጸው፡- ኢሣትም በሃገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚደረገውን ትግል በማገዝ ረገድና በአምባ ገነን ገዢዎች ሃሳቡን በነጻ የመግለጽ መብቱን ላጣው ሕዝባችን ነጻነት የሚያበረክተውን አስተዋጾ አመላክተዋል።

አቶ አበበ አጠር ያለ ንግግራቸውን ያጠናቀቁት የኢሣት ሰብሳቢ ዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻ ከሚገኙበት ሃገር በቀጥታ ኢሣትን በመወከል ለዝግጅቱ ታዳሚ መልዕክት እንዲያስተላልፉ በመጋበዝ ነበር።

ዳኛ ወልደ ሚካኤል በስካይፒ አማካኝነት በቀጥታ ለዝግጅቱ ታዳሚ ባስተላለፉትም መልዕክት፡- በሜልበርን የሚገኘው ኢትዮጵያዊ በራሱ አነሳሽነት ኢሳትን ለመርዳት ላደረገው እንቅስቃሴ ኢሣት ከፍተኛ አድኖቆት እንዳለው ገልጸው፡- ይህንን የተቀደሰ ተግባር ከግብ ለማድረስ የተንቀሳቀሰውን ዲሞክራሲ ለኢትዮጵያ ድጋፍ ቡድን አባላት አመስግነዋል።

ኢሳትን ለመርዳት በራስ አነሳሽነት እንቅስቃሴ በማድረግ የሜልበርን ኢትዮጵያዊ የመጀመሪያው ነው! ሲሉ አድንቆታቸውን የገለጹት ዳኛ ወልደ ሚካኤል አክለውም፡- ኢሣት በጥቂት ሰዎች ጥረት ቢጀመረም የቀጣይነቱ ተስፋ የተጣለው በሁሉም ኢትዮጵያዊ ላይ ነውና ድጋፍችሁ አይለየን ሲሉ የአደራ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ዳኛ ወልደ ሚካኤል ቀጥለውም፡- ኢሳት እንቅስቃሴውን በተሳካ መልክ ለማከናወን እንዲያመቸው፤ ኢትዮጵያዊያን በሚገኙበት በተለያዩ ሀገራት ወኪሎች እንዲኖሩት እያደረገ መሆኑንና በሜልበርንም ወ/ሪት ገነት መወከሏን ገልጸዋል።ከዚህም በተጨማሪ ከኢሣት እንቅስቃሴ ጋር ለሚገናኙ ጉዳዮች ሁሉ፡-የኢሣት ግንኙነት ኃላፊ የሆኑትን አቶ ከንፉ አሰፋን (የ EMF አዘጋጅ) ማነጋገር እንደሚቻልም፤ ጠቁመዋል።

ዳኛ ወልደ ሚካኤል ኢሳትን በመወከል ለሜልበርን ኢትዮጵያዊ ያስተላለፉትን መልዕክት የቋጩት የኢሣትን እንቅስቃሴ በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉ ለመመለስ ፈቃደኛ መሆናቸውን በመግለጽ ነበር።

በዚሁ መሰረትም ጥቂት የማይባሉ ጥያቄዎች ተሰንዝረው በዳኛ ወልደ ሚካኤል በቂ ማብራሪያ የተሰጠባቸው ሲሆን፡-በተለይ የኢሳትን ቀጣይነት በተመለከተና በተደጋጋሚ የደረሰበትን አፈና ተመርኩዞ ለቀረበው ጥያቄ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የዳኛ ወልደ ሚካኤል መልዕክት እንደተጠናቀቀ ፡ በፕሮግራሙ ቅደም ተከተል መሰረት ለእንግዶች የተዘጋጀው የራት ግብዣ ቀጥሏል። ከራት ግብዣው በተጓዳኝም ስለ ኢሣት እንቅስቃሴና የዝግጅት ይዘት ግንዛቤ በሚሰጥ መልክ የተዘጋጀው የቪዲዮ ቅንብር በትልቅ ስክሪን ሲታይ አምሽቷል።

በመጨረሻም በተደረገው የዕርዳታ ማሰባሰብ ሥነ - ሥርአትና ከመግቢያ ትኬት ሽያጭ በድምሩ ከ 6100 የአውስትራሊያ ዶላር በላይ እንደተገኘ የድጋፍ ኮሚቴው አባላት ለተሰብሳቢው እንግዶች ገልጸው በዚሁ የእርዳታ ማሰባሰቢያው ዝግጅት ተጠናቋል።

በቋጠሮ ዝ/ክ